ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ

Wisdom at the source of the Blue Nile

# የሳይንስ ኮሌጅ የ2006 በጀት ዓመት የ9 ወር ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት

ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ

መጋቢት 2006 ዓ.ም

# ማውጫ


ማውጫ ........ 0

I. መግቢያ ........ 2

II. የኮሌጁ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች ........ 5

2.1. ተልዕኮ ........ 5

2.2. ራዕይ ........ 5

2.3. እሴቶች ........ 5

III. የ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ........ 6

3.1. ከመልካም አስተዳደር አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ........ 6

3.2. ከአመለካከት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ........ 7

3.3. ከክህሎት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ........ 8

3.4. ከአደረጃጀትና አሰራር አንጻር የተከናወኑ ተግባራት ........ 9

3.5. የኮርስ አስተዳደር ........ 12

3.6. የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት ........ 14

3.7. ምርምር ........ 14

3.8. ማኅበረሰብ አገልግሎት ........ 17

IV. በእቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች ........ 17

V. ለወደፊት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 17

VI. ማጠቃለያ ........ 18

VII. የሳይንስ ኮሌጅ የ2006 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ........ 19

# I. መግቢያ

የአሁኑ ሳይንስ ኮሌጅ መምህራንን በዲፕሎማና ቀጥሎም በዲግሪ ደረጃ እያሰለጠነ ሲያስመርቅ ከነበረውና በኋላም የትምህርት ፋኩልቲ ተብሎ ከተደራጀው ከድሮው ፔዳጎጅ አካዳሚ የተወለደ ኮሌጅ ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲው በተካሄደው ሥራን መልሶ የማደራጀት ጥናት ወቅት የቀድሞው የትምህርት ፋኩልቲ ወደ ተለያዩ የሥራ ክፍሎች ሲከፋፈል በአገር አቀፍ ደረጃ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ የትምህርት ዘርፎች የተሰጠውን ትኩረት ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተፈጥሮ ሳይንስ ከ2001 ዓ.ም. ጀምሮ በኮሌጅ ደረጃ እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

ሳይንስ ኮሌጅ በአሁኑ ጊዜ 222 መምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች አሉት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 132 መምህራንና 24 የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች በሥራ ላይ ያሉ ናቸው፡፡ በስራ ላይ ካሉ መምህራን መካከል 37 (29%) የዶክትሬት ዲግሪ፣ 89 (67%) የማስትሬት ዲግሪና፣ 6 (4%) የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው ናቸው፡፡ ከቴክኒካል አሲስታንቶች መካከልም 22ቱ (88%) የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪና ሌሎች 3 (12%) ዲፕሎማ (10+4) ያላቸው ናቸው፡፡

ቀሪዎቹ 68 የሚሆኑት ደግሞ በትምህርት ላይ ያሉ ሲሆን 4ቱ (7%) ለድህረ ዶክትሬት 56ቱ(67%) ለዶክትሬት ዲግሪ እና 17ቱ (27%) ደግሞ ለማስትሬት ዲግሪ የሚያበቃቸውን ትምህርት በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡ አዲስ ዕድል አግኝተው የሚማሩትን ሳይጨምር በትምህርት ላይ ያሉት ትምህርታቸውን አጠናቀው ሲመለሱ የዶክትሬት ዲግሪ ያላቸው መምህራን ብዛት ወደ 44% ያድጋል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ በየትምህርት ክፍሎች ያለው የመምህራንና ቴክኒካል ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች መረጃ ሲታይ፣

*በሳይንስ ኮሌጅ በስራ ላይ ያሉ መምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች (መጋቢት 2006)*

| የትምህርት ክፍል | ፕሮፌሰር | ተባባሪ ፕሮፌሰር | ረዳት ፕሮፌሰር | ሌክቸረርና ረ/ሌክቸረር | ረዳት ምሩቅ | የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ባዮሎጂ | 0 | 2 | 10 | 11 | 0 | 9 | 32 |
| ኬሚስትሪ | 0 | 0 | 9 | 16 | 1 | 9 | 35 |
| ኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ | 0 | 0 | 0 | 5 | 1 | 0 | 6 |
| ኧርዝ ሳይንስ | 0 | 0 | 0 | 7 | 1 | 1 | 9 |
| ሒሳብ | 1 | 0 | 7 | 32 | 0 | 1 | 41 |
| ፊዚክስ | 0 | 3 | 4 | 11 | 3 | 4 | 25 |
| ስታቲስቲክስ | 0 | 0 | 1 | 7 | 0 | 1 | 9 |
| ድምር | 1 | 5 | 31 | 89 | 6 | 25 | 157 |

*በሳይንስ ኮሌጅ በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን (መጋቢት 2006)*

| የትምህርት ክፍል | ለድህረ ዶክትሬት ዲግሪ | ለዶክትሬት ዲግሪ | ለማስትሬት ዲግሪ | ድምር |
|---|---|---|---|---|
| ባዮሎጂ | 1 | 11 | 4 | 16 |
| ኬሚስትሪ | 3 | 13 | 2 | 18 |
| ኢንዱስትሪል ኬሚስትሪ | 0 | 1 | 5 | 6 |
| ኧርዝ ሳይንስ | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ሒሳብ | 1 | 10 | 1 | 12 |
| ፊዚክስ | 0 | 8 | 1 | 9 |
| ስታቲስቲክስ | 0 | 1 | 4 | 5 |
| ድምር | 5 | 44 | 17 | 66 |

ይህ አሃዝ በስትራቴጂክ ዕቅዳችን የተቀመጠውን የዶክትሬት፣ የማስትሬትና የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸው መምህራን ስብጥር ግብ ቀድመን ማሳካት የምንችል መሆኑን ከማሳየቱም በተጨማሪ የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥና ዩኒቨርሲቲውን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለማድረግ ያለንን ራዕይ ለማሳካት ከፍተኛ አቅም የሚፈጥርልን ይሆናል፡፡

ከስልጠና መስኮች አንጻር ኮሌጁ በ7 የቅድመ ምረቃ (ባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ኢንዱስትሪያል ኬሚስትሪ፣ ኧርዝ ሳይንስ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስና ስታቲስቲክስ)፣ በ5 የሁለተኛ ዲግሪ (በባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስና ማቴሪያል ሳይንስ የተለያዩ ስፔሺያላዜሽኖች) እና በአንድ የሶስተኛ ዲግሪ (ዶክትሬት ዲግሪ በስፔስ ፊዚክስ መስክ) መርሐ ግብሮች በማሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡

ኮሌጁ የትምህርት ተደራሽነትን ከማጋገጥ አኳያ በቅድመ ምረቃ በመደበኛ፣ በክረምት፣ በተከታታይና በርቀት ትምህርት ፕሮግራሞች 4705 ተማሪዎችን ተቀብሎ በማሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡ ከዚህ አኳያ በቅድመ ምረቃ መደበኛ ፕሮግራም 1459 (ከእነዚህ ውስጥ 36% ሴት ተማሪዎች)፣ በክረምት 1672 (ከእነዚህ ውስጥ 20% ሴት ተማሪዎች)፣ በተከታታይ ትምህርት 32 (ከእነዚህ ውስጥ 28% ሴት ተማሪዎች) እና በርቀት 1352 (ከእነዚህ ውስጥ 27% ሴት ተማሪዎች) ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ነው፡፡ በማስተርስ ዲግሪ ፕሮግራም ደግሞ በመደበኛ 86 (ከእነዚህ ውስጥ 16% ሴት ተማሪዎች) እና በክረምት 704 (ከእነዚህ ውስጥ 17.5% ሴት ተማሪዎች) በድምሩ 801 ተማሪዎችን እንዲሁም በPhD ደረጃ 6 (ሁሉም ወንድ ተማሪዎች) ተማሪዎችን በማሰልጠን ላይ ነው፡፡ ኮሌጁ በቅድመ ምረቃ በድምሩ 4705 እና ድህረ ምረቃ በድምሩ 801 በጠቅላላው 5506 ተማሪዎች አሉት፡፡

**የቅድመ ምረቃ ተማሪዎች (መጋቢት 2006 ዓ.ም)**

| ፕሮግራም | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| መደበኛ | 933 | 526 | 1459 |
| ክረምት | 1351 | 321 | 1672 |
| የማታ | 23 | 9 | 32 |
| ርቀት | 1150 | 392 | 1542 |
| ድምር | 3457 | 1248 | 4705 |

**የድህረ ምረቃ ተማሪዎች (መጋቢት 2006 ዓ.ም)**

| ፕሮግራም | ወንድ | ሴት | ድምር |
|---|---|---|---|
| መደበኛ | 72 | 14 | 86 |
| ክረምት | 581 | 123 | 704 |
| ድምር | 653 | 137 | 801 |

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ሀገራችን የነደፈችውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ እውን ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ጥናቶችና ምርምሮች በማካሄድ፣ ችግር ፈች የሆነ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ የማኅበረሰብ አገልግሎት በመስጠት፤ የሀገራችንን ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ልማት ለማፋጠን የበኩሉን ጥረት እያደረገ የሚገኝ የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው፡፡ ከተቋሙ አካል አንዱ የሆነው የሳይንስ ኮሌጅ ከዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈፀምና ራዕዩን ለማሳካት ከዩኒቨርሲቲያችን የረጅም ጊዜ ዕቅድ ጋር የተጣጣመ ዕቅድ በማውጣት ወሳኝ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡ የትምህርት ተደራሽነትን፣ ጥራትና አግባብነትን ለማረጋገጥና ለአካባቢው ማኅበረሰብ ፋይዳ ያለው የማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአጭርና የረዥም ጊዜ ዕቅድ በማውጣት ሥራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በ2006 ዓ.ም ሊከናወኑ ከተያዙት አበይት ተግባራት መካከል **አግባብነት እና ጥራት ያለው ትምህርት በቅድመ ምረቃና በድህረ ምረቃ መስጠት፣ ችግር ፈቺ ምርምር ማድረግና ማኅበረሰብ አገልግሎት መስጠት እና እንዲሁም በኮሌጁ መልካም አስተዳደር ማስፈን** የሚሉት ጥቂቶቹና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በ2006 በጀት ዓመት ያለፉት 9 ወራት ኮሌጁ ከእቅድ አኳያ የነበረው አፈጻጸም እንደ አጠቃላይ ሲታይ አበረታች ደረጃ ላይ የሚገኝ ቢሆንም ካለው አቅም አንጻር አሁንም የበለጠ መስራት እንደሚቻል አመላካች ጉዳዮች ያሉ በመሆኑ በቀሪዎቹ ሶስት ወራት ያለንን ሃይል በማረባረብ የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ በተደራጀ አግባብ የበለጠ ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል፡፡

ከዚህ አንጻር በዚህ ሪፖርት በ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ሶስት ሩብ ዓመታት የተከናውኑ ዐበይት ተግባራትንና በቀጣይ ሶስት ወራት ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን ከዕቅድ አንጻር ለማመላከት ተሞክሯል፡፡

# II. የኮሌጁ ራዕይ፣ ተልዕኮ እና ዕሴቶች

## 2.1. ተልዕኮ

በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ከሚገኙ ተቋማት አንዱ የሳይንስ ኮሌጅ ነው፡፡ ኮሌጁ የዩኒቨርሲቲው አንድ አካል እንደ መሆኑ አገሪቱ የምትፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት በማፍራት፣ አገራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ጥናትና ምርምሮች በማድረግና የማህበረሰብ አገልግሎት በመስጠት ለአገራዊ ብሎም ዓለማቀፋዊ ዕድገት ጉልህ አስተዋጾኦ የማድረግ ተልዕኮን አንግቦ ይንቀሳቀሳል፡፡

## 2.2. ራዕይ

የሳይንሳ ኮሌጅ የኒቨርሲቲያችን **"እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር በ2017 ዓ.ም. በአፍሪካ ከሚገኙ አስር ግንባር ቀደም የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ መሆን"** የሚለውን ራእዕ ለማሳካት ይሰራል፡፡

## 2.3. እሴቶች

ዩኒቨርሲቲያችን ያስቀመጣቸውን እሴቶች

- Quality
- Discourse,
- Innovation,
- Integrity,
- Democratic culture,
- Social responsibility

ለማዳበር ሳይንስ ኮሌጅ የድርሻውን ለመወጣት ቁርጠኛ ሆኖ ይሰራል፡፡

# III. የ2006 በጀት ዓመት የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወራት ዕቅድ አፈጻጸም

## 3.1. ከመልካም አስተዳደር አንጻር የተከናወኑ ተግባራት

### የመምህራና ሰራተኞች የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች

ከመምህራን አኳያ በዕቅድ ተይዘው የነበሩ የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች የመምህራን የቢሮ ችግር መፍታት፣ የመምህራንን የወንበር፣ የጠረጴዛና የኮምፒዩተር ፍላጎት ማሟላት፣ከመምህራን ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ግልጽና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት፣ የአካዳሚክ ስታፍን የእድገት መመሪያና ደንቦች መሰረት በማድረግ መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንቶች እድገት እንዲያገኙ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ

- የመምህራን የቢሮ ችግር መፍታትን በተመለከተ እንደሚታወቀው ችግሩ ከኮሌጁ አቅም በላይ በመሆኑ በኮሌጁ በኩል ለበላይ አመራሩ በተደጋጋሚ ጊዜ ጥያቄው የቀረበ ቢሆንም፣ እንዲሁም በበላይ አመራሩም በኩል ችግሩ ተገቢ ግንዛቤ ያገኘ ቢሆንም ችግሩ እስካሁን አልተፈታም፡፡ በቅርቡ የዩኒቨሲቲው አስተዳደር አዲስ ወደ ተሰራው የሰአተዳደር ሕንጻ (የጥበብ ሕንጻ = “Wisdom Tower”) ሲዛወር የተወሰነ መፍትሄ እንደሚገኝ ተስፋ ይደረጋል፡፡
- የመምህራንን የወንበር፣ የጠረጴዛና የኮምፒዩተር ፍላጎት ማሟላትን በተመለከተ የእነዚህ ቁሳቁሶች ግዥ በማዕከላዊ የግዥ ኬዝ ቲም እየተገዛ በመሆኑ ኮሌጆች ግዥ እንዳይፈጽሙ በመታገዱና ግዥውም ያልፈተፈጸመ በመሆኑ ችግሩ አልተፈታም፡፡ የግዥዎች አለመፈጸም በመምህራን አሰራር ላይ ከሚያስከትለው ጫና በተጨማሪ በዚህ ዓመት ለመክፈት ታቅደው የነበሩ የኮምፒዩተር ቤተ ሙከራዎች ባለመከፈታቸው በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳደረ በመሆኑ የማዕከላዊ ግዥ ኬዝ ቲም ግዥውን በአስቸኳይ ፈጽሞ ዕቃዎቹን ሊያስረክበን ይገባል፡፡
- ከመምህራን ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ግልጽና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠትንና የአካዳሚክ ስታፍን የእድገት መመሪያና ደንቦች መሰረት በማድረግ መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንቶች እድገት እንዲያገኙ ማድረግን በተመለከተ ለቀረቡ ሕጋዊ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሾች በወቅቱ የተሰጡ ሲሆን መስፈርቱን ላሟሉ መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንቶች እድገት ተሰጥቷል፡፡

### የተማሪዎች የመልካም አስተዳደር ጉዳዮች

ከተማሪዎች አኳያ ኮሌጁ በ2006 በጀት ዓመት የተማሪዎች ተወካዮች ተማሪ ተኮር በሆኑ ውሳኔዎች እንደሳተፉ ማድረግ፣ በአካዳሚክ አድቫይዘር የማማከር ችግር (ስህተት) የሚነሱ ችግሮችና ቅሬታዎችን መቀነስ፣ ለሚቀርቡ የትምህርት ማስረጃ ጥያቄዎች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ መስጠት፣ ተማሪዎች ለሚያቀርቡአቸው ጥያቄዎች አፋጣኝ ሕጋዊ ምላሽ በመስጠት የተማሪዎችን እርካታ መጨመር፣ ለተመራቂ

ተማሪዎች መረጃ (Temporary Degree) በወቅቱ መስጠት የሚሉ ተግባራትን አቅዶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዚህም መሰረት፣

- የተማሪ ተወካዮች በኮሌጁ የአካደሚክ ካውንስል አባል በመሆናቸው በውሳኔዎች ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ የሚሆኑ ሲሆን የኮሌጁ የስራ ኃላፊዎች ከየክፍል ተወካዮች ጋር የትምህርት አስተዳደሩን በተመለከተ በየሁለት ሳምንቱ መደበኛ ስብሰባ ስለሚያደርጉ በትምህርቱ ሂደትም ተማሪዎች ቀጥተኛ ተሳታፊዎች ናቸው፡፡
- በአካዳሚክ አድቫይዘር የማማከር ችግር (ስህተት) ምክንያት አሁንም ቢሆን አልፎ አልፎ ችግሮች የሚከሰቱ ቢሆንም ውይይት በማድረግ ችግሮቹ በኃላ መልኩ እንዲቀንሱ ተደርጓል፡፡ ችግሮች ሲከሰቱም በኮሌጁ የአካዳሚክ ካውንስል እየታዩ ተገቢ መፍትሄ ያገኛሉ፡፡ በሬጅስራር ክፍላችን ካለው የመረጃ አያያዝ ክፍተት ጋር በተያያዘ መመረቅ የሚገባቸው ተማሪዎች የምረቃ ጊዜ የሚራዘምበት ሁኔታዎች አሁንም ስላሉ መልካም የመሻሻል ጅምሮች ቢኖሩም ኮሌጃችን በቀጣይ ትኩረት ሰጥቶ የሚሰራው አንዱ ተግባር የሬጅስራር ክፍል አሰራርን መከታተል ይሆናል፡፡

## 3.2. ከአመለካከት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት

### የተማሪዎችን አመለካከት በማሻሻል ረገድ የተሰሩ ስራዎች

የዩኒቨርሲቲውና የኮሌጁ ዋና ደንበኛና ባለድርሻ የሆኑት ተማሪዎች ለዩኒቨርሲቲው ራዕይና ተልዕኮ መሳካት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ይህን ወሳኝ የሆነ ሚናቸውን ገንቢ በሆነ ሁኔታ እንዲጫወቱ ካስፈለገ በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማርና ሌሎች ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ በሚሰሩ ስራዎችና በውሳኔዎች ላይ ተሳታፊ ሊሆኑና ትክክለኛ የሆነ አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በመሆኑም ኮሌጁ በ2006 በጀት ዓመት ከያዛቸው ዕቅዶች መካከል ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ወቅት ሊይዙት ስለሚገባ ሥነምግባርና ስለመማር ማስተማር ሂደት ግንዛቤ መፍጠርና ተማሪዎችን በተደራጀ አግባብ በመደበኛነት ማወያየት ይገኝበታል፡፡

በዚህ መሰረት የክረምት የቅድመ ምረቃ እና የመደበኛና የክረምት የድህረ ምረቃ ተማሪዎችን በመማር ማስተማር፣ ምርምርና በችግሮቻቸው ዙሪያ አወያይተናል፡፡ ባገኘነው ግብዓት መሰረትም ለችግሮቻቸው መፍትሄዎች ተሰጥተዋል፡፡ የመደበኛ ቅድመ ምረቃ ተማሪዎች ከክረምት ዕረፍት ተመልሰው ምዝገባ እንዳካሄዱ ስለ 2005 ዓ.ም. ክንውን ጥንካሬና ድክመትና ስለ 2006 የትኩረት አቅጣጫዎች እንዲሁም ስለ ልማት ዲሞክራሲና የሃይማት አክራሪነት ውይይት ለማድረግ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ በተያዘው ዕቅድ መሰረት ኮሌጁም ተማሪዎችን በስፋት አወያይቶ ከተማሪዎች ጋር በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡ በሁለተኛው አጋማሽ መጀመሪያ ላይም በመጀመሪያው አጋማሽ ስለተከናወኑ ተግባራትና ያጋጠሙ ችግሮች፣ ስለቀጣይ ወራት የትኩረት አቅጣጫዎችና ስለመማር መመራመርና መተግበር ቡድኖች አሰራርና ዓላማ ውይይት ተደርጓል፡፡ ለአንደኛ ዓመት ተማሪዎችም በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት መጀመሪያ ላይ

ስለሞዱላራይዜሽን፣ አካዳሚክ ሬጉሌሽን፣ እና የመማር መመራመርና መተግበር ቡድኖች አሰራርና ዓላማ እንዲሁም በሁለተኛው አጋማሽ መጀመሪያ ላይም በመጀመሪያው አጋማሽ ስለተከናወኑ ተግባራትና ያጋጠሙ ችግሮች፣ ስለቀጣይ ወራት የትኩረት አቅጣጫዎችና ስለመማር መመራመርና መተግበር ቡድኖች አሰራርና ዓላማ ውይይት ተደርጓል፡፡

ይህም በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ሰላማዊ የመማር ማስተማር ሂደት ታይቷል፡፡ ተማሪዎች ጥያቄያቸውን በሰላማዊ ሁኔታ የማቅረብ መልካም ጅማሮ አለ፡፡ በተለያዩ ጊዜያት ከተማሪዎች ጋር በሚደረጉ ውይይቶችና በተወሰነ ደረጃም ቢሆን በአንዳንድ መምህራን ላይ የሚቀርቡ የተማሪ ቅሬታዎች ሲጤኑ ከዕውቀት ይልቅ ውጤት (በነጥብ የሚገለጽ) ላይ የማተኮር አዝማሚያዎች ይታያሉ፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ዕውቀት ፈላጊነት ላይ ትኩረት እንዲያደርጉ ኮሌጃችን ሞዴል የመውጫ ፈተና በመስጠት ተማሪዎቹ በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ስላካበቱአቸው ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከቶች አንጻር ራሳቸውን እንዲመለከቱ ለማድረግ በመስራት ላይ እንገኛለን፡፡

### የመምህራንን አመለካከት በማሻሻል ረገድ የተሰሩ ስራዎች

የኮሌጁ መምህራንና ኮርስ ቼሮች በሞጁላር የትምህርት አሰጣጥ፣ ተግባር ተኮር ትምህርት፣ ተከተታይ ምዘናና ግብረ መልስ እንዲሁም ስለኮርስ ቼሮች ተግባርና ኃላፊነት ውይይት በማድረግ የጋራ መግባባት ላይ መድረስ ሌላው ኮሌጁ ባሳለፍናቸው ወራት አቅዶ ተግባራዊ ያደረገው ሥራ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ከጊዜ ወደ ጊዜ የክፍልና የኮርስ አሸፋፈን፣ተከታታይ ምዘናና የምዘና ግብረ መልስ አፈጻጸም ከፍተኛ ለውጥ እያሳየ መጥቷል፡፡ ሆኖም አሁንም ቢሆን ከመምህርነት ስነ ምግባር ኃላፊነትና አኳያ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ቆይታቸው ተገቢውን ዕውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት ይዘው እንዲወጡ ትከረት ሰጥቶ መርዳትና ግብረ መልስ መስጠት ላይ ክፍተቶች አሉ፡፡ በታሪክ አጋጣሚ ወደ ዩኒቨርሲቲያችን የመጡ ተማሪዎች ምንም ዓይነት አካዳሚያዊም ሆነ ስነ ምግባራዊ ደረጃ ላይ ቢሆኑም ተገቢ ድጋፍ በማድረግና አርኣያ ሆኖ በመጀኘት ተማሪዎቻችን ብቃትና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው፣ ለአገርና ለወገን ጠቃሚ ዜጎች ሆነው እንዲወጡ መምህራንና በአጠቃላይም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የበኩሉን ድርሻ መወጣት አለበት፡፡

የአቻ ለአቻ ትምህርት (Peer Learning) ጽንሰ ሃሳብና የአሰራር መመሪያዎችን በተመለከተ ከትምህርትና ሥነ ባህሪ ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በመተባበር ለ69 የኮርስ ባለቤቶች፣ የክፍል ኃላፊ መምህራንና ተማሪዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት መጀመሪያ ላይም ከኮሌጁ መምህራን ጋር በመጀመሪያው አጋማሽ ስለተከናወኑ ተግባራትና ያጋጠሙ ችግሮች፣ ስለቀጣይ ወራት የትኩረት አቅጣጫዎችና ስለመማር መመራመርና መተግበር ቡድኖች አሰራርና ዓላማ ውይይት ተደርጓል፡፡

## 3.3. ከክህሎት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት

በያዝነው በጀት ዓመት ከክህሎት አንጻር መምህራን ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር የተገናኘ ስልጠና (Subject matter Knowledje) እንዲያገኙ ማድረግ፣ መምህራን የምርምርና መረጃ ትንተና ዘዴዎች

መሠረታዊ ክህሎትና እውቀት እንዲያገኙ ስልጠና መስጠት፣ መምህራን የማስተማር ክህሎት HDP ስልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ መምህራን ወደ ተለያዩ ተቋማት ሄደው የልምድ ልውውጥ እንዲያደርጉ ማድረግ፣ ለኮሌጁ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች (ላብራቶሪ አሲስታንቶች) ስለደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ያለመ ስልጠና መስጠት ለኮሌጁ የአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች (ጸሃፊዎች፣ የደንበኞች አገልግሎት ሰራተኞች፣ የቤተ መጻህፍት ሰራተኞች) የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተመደቡበት ኃላፊነት የሚያስፈልገውን ሙያ እንዲያካብቱ ያለመ ስልጠና መስጠት የሚሉ ዕቅዶች ነበሩን፡፡

የኮሌጃችን መምህራንና የድህረ ምረቃ ተማሪዎቻችን ስለምርምር አሰራር የክህሎት ማዳበሪያ ስልጠና እንዲያገኙ በታቀደው መሰረት በአቅም ግንባታ ማዕከል አስተባባሪነት በኮሌጃችን የስታቲስቲክስ ትምህርት ፕሮግራም መምህራን ምርምር ለሚሰሩ የኮሌጃችንና የሌሎች ኮሌጆች መምህራንና የድህረ ምረቃ ተማሪዎች በመሰረታዊ የስታቲስቲካዊ መረጃ ትንተና ዘዴዎችና ለዚሁ ሥራ የሚረዱ ስታቲስቲካዊ ሶፍትዌሮች ላይ በተለያዩ ዙሮች የክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ ከሰልጣኝ መምህራን በተገኘው ግብረ መሰረት ስልጠናው ስለምርምር ተጨማሪ አቅም የሚፈጥር ነው፡፡  በተጨማሪም ለ 8 መምህራን በGIS application ላይ የክህሎት ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ለመምህራን የማስተማር ክህሎት HDP ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ በታቀደው መሰረት ስልጠናው ከትምህርትና ስነ ባህርይ ሳይንስ ፋካልቲ ጋር በመተባበር ተሰጥቷል፡፡

በስታቲስቲክስ ትምህርት ክፍል በኩል ለ9 መምህራን የSTATA, R እና SAS ስልጠና ለመስጠት ተይዞ በነበረው ዕቅድ መሰረት ጥያቄው ለጥራት ማሻሻያና ቁጥጥር ዳይሬክተር ጽ/ቤት ቀርቦ ውሳኔውን በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡

## 3.4. ከአደረጃጀትና አሰራር አንጻር የተከናወኑ ተግባራት

### መማር፣ መመራመርና መተግበር ቡድኖች

በኮሌጃችን 7 የትምህርት ክፍሎች፣ 32 ሴክሽኖችና 32 የኮርስ ቡድኖች አሉ፡፡ በዚህም መሰረት አንድ የኮሌጅ አካዳሚክ ካውንስል አደረጃጀት፣ 7 የትምህርት ክፍል አደረጃጀቶች፣ 32 የኮርስ ቡድንና 247 የተማሪዎች መማር፣ መመራመርና መተግበር ቡድን አደረጃጀቶች ተፈጥረዋል፡፡ የተፈጠሩትን አደረጃጀቶች ዓላማና አሰራር በተመለከተ የተዘጋጀውን የአሰራር መመሪያ ለማስተዋወቅ ለሁሉም አደረጃጀቶች ኦሬንቴሽን የተሰጠ ሲሆን ተግባራዊነቱ ትኩረት ተሰጥቶት ክትትል እየተደረገበት ነው፡፡

ይህም በመሆኑ በአሁኑ ጊዜ የኮሌጅ አካደሚክ ካውንስልና የትምህርት ክፍል መማር፣ መመራመርና መተግበር (መመመ) ቡድኖች በወጣው መመሪያ መሰረት መማር ማስተማር፣ ምርምር፣ ማህበረሰብ አገልግሎት ተግባራት ላይ ትኩረት በማድረግ መደበኛ ውይይት ያደርጋሉ፡፡ ከተፈጠሩት 247 የተማሪ

መመመ አደረጃጀቶች መካከልም 245 (99%) የሚሆኑት ሳምንታዊ ዕቅድ እያወጡ መወያየት ጀምረዋል፡፡ በተደረገው ክትትል የተወሰኑ ቡድኖች ባወጡት ዕቅድ መሰረት እየተገናኙ የቡድን ስራዎች የሚሰሩና የሚያጠኑ ቢሆንም አብዛኞቹ ቡድኖች ዕቅድ ከማዘጋጀት ባለፈ በሙሉ ትኩረት በጋራ እየተዳዱ መስራት ላይ ብዙ የሚቀር ነገር እንዳለ መረዳት ተችሏል፡፡ በሌላ መልኩ የኮርስ ቡድኖች አደረጃጀቶች በመመሪያው አፈጻጸም ላይ ያላቸው አፈጻጸም ከቡድን ቡድን የተለያየ ቢሆንም እንደአጠቃላይ ግን አጥጋ የሚባል አይደለም፡፡ በቀጣይ ወራት ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ ይሆናል፡፡

## የመረጃ አያያዝና አደረጃጀት

### የተማሪዎች መረጃ አያያዝ

በክረምቱ ወቅት ማጠናቀቂያ ላይ 396 የቅድመ ምረቃ እና 54 ድህረ ምረቃ የክረምት ተማሪዎች ያስመረቅን ሲሆን፣ በበጀት ዓመቱ 464 አዲስ ገቢየመደበኛ ቅድመ ምረቃና 35የድህረ ምረቃ መደበኛተማሪዎችን ተቀብለን የህይወት ታሪክ  ፎርም የማስሞላት፣ በስማቸው ፋይል የመክፈት፣ ሴክሽን የመመደብና መታወቂያ የመስጠት ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ እንዲሁም በ2006 ዓ.ም. 220አዲስ ገቢ የርቀት ተማሪዎች መረጃ ከሴንተር አስተባባሪዎች በመረከብ ፋይል ተከፍቶላቸዋል፡፡ ከተማሪዎች መረጃ አውቶሜሽን አንጻር 95% የሚሆኑት የቅድመ ምረቃ መደበኛ፣ ክረምት፣ ተከታታይና የርቀት ተማሪዎችን የህይወት ታሪክወደ SIMS ገብቷል፡፡

ከተማሪዎች የትምህርት ማስረጃ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ባለፉት ወራት ትኩረት ሰጥተን ከሰራናቸው ተግባራት መካከል ከ2002 እስከ 2005 ዓ.ም.ድረስ ያሉ የተመራቂ ተማሪዎችን መረጃ በማሟላት ለዋናው ሬጅስትራር ማስረከብ ሲሆን ይህ ሪፖርት እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስ ከ2002 እስከ 2004 ያሉ ፋይሎችን ማስተላለፍ ችለናል፡፡ ይህ ትልቅ ውጤት ነው፡፡ በቀሪዎቹ ወራት የ2005 ዓ.ም. ተመራቂ ተማሪዎችን መረጃ በማሟላት ለዋናው ሬጅስትራር ለማስረከብ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን፡፡

### የመምህራን መረጃ አያያዝ

በስራ ላይና በትምህርት ላይ ያሉ መምህራንን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃ ተይዟል፡፡ ይሁንና የመምህራንን ዝርዝር መረጃ (Profile) ወደ ኮሌጁ ድረገጽ ለመጫን እየተደረገ ያለው ያላሰለሰ ጥረት አበረታች ለውጥ እያሳየ ቢሆንም አብዛኞቹ የባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪና ፊዚክስ መምህራንን መረጃ ገና አልገባም፡፡

### የኮሌጁ ድረገጽ ወቅታዊ ማድረግ

የኮሌጁ ድረገጽ የተሰራው በዚህ በጀት ዓመት መጀመሪያ ሲሆን አስፈላጊ መረጃዎችና ዜናዎችን በመጫን ወቅታዊ የማድረግ ተግባራት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ያለ ቢሆንም አሁንም አንዳንድ ያለገቡ መረጃዎች ያሉ በመሆኑ በቀጣይም በትኩረት የምንሰራው ስራ ነው፡፡

## የኮሌጁ ቤተ ሙከራዎች አሰራር

ቤተ ሙከራዎቻችንን በተመለከተ ታቅደው የነበሩ ተግባራት ስለካይዘን አሰራር ለመምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፣ በቤተ ሙከራ ስቶሮች የሚገኙ ንብረቶችን ቆጠራ ማድረግና በኮምፒዩተር መዝግቦ መያዝ፣ የቤተሙከራዎች የስራ ማንዋል ማዘጋጀት የኮሌጁን ቤተ ሙራዎች ፓርቲሽን ማሰራት፣ መደበኛ በሆነ ሁኔታ የቤተ ሙከራ ማቴሪያሎች ጽዳት እና ቆጠራ ማካሄድ፣ ለቤተ ሙከራ መምህራንና ረዳቶች ተከታታይ የግምገማና ክትትል ሥርዓት መዘርጋትና ክትትል ማድረግ፣ የቤተ ሙከራዎችን አሰራር የተመለከተ የስራ መመሪያ (Guideline) ማዘጋጀት፣ የቤተ ሙከራ ባለቤት ፕሮፌሰሮች ምደባ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ አንጻር ከፊዚክስ፤ ባዮሎጂና ኬሚስትሪ ት/ት ክፍሎች 36 የሚሆኑ የላቦራቶሪ ኮርሶች ማኑዋል የሌላቸው መሆናቸው ታውቆ ለያንዳንዱ ኮርስ ማኑዋል መምህር ተመድቦ ማኑዋሎቹ እየተዘጋጁ ናቸው፡፡ት/ት ክፍሎች ጥራቱን የጠበቀ የተግባር ት/ት ለመስጠት እንዲችሉበየክፍሎቻቸው ያሉና የሌሉ የመሳሪያም ሆነ የኬሚካል የመለየት ስራ ከተሰራ በኋላGAP Analysis ተሰርቶ የማይሰሩና የተጓደሉ ማሳሪያዎችና ኬሚካሎችለማሟላት የሚያስችል የግዥ ስፔሲፊኬሽን ተዘጋጅቶ የግዥ ጥያቄ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት የተወሰኑ መሳሪያና ኬሚካሎች በግልጽ ጨረታና የተወሰኑት ደግሞ ከፌዴራል የግዥ ኤጀንሲ ባገኘነው ፈቃድ መሰረት በውስን ጨረታ ግዥ ለማከናወን ከፍተኛ ጥረት ስናደርግ የከረምን ቢሆንም በግዥ ክፍሉ የአፈጻጸም ችግር ምክንያት ግዥው እስካሁን አልተፈጸመም፡፡ የግልጽ ጨረታው ሰነድ ከተከፈተ ወራት የተቆጠሩ ቢሆንም ውጤቱን በትእግስት እየተጠባበቅን እያለን የወደቀበት ምክንያት ምን እንደሆነ እና ተጠያቂውስ ማን እንደሆነ አውቀን ድጋሚ ተመሳሳይ ሁኔታ እንዳያጋጥመን ለመማር በማያስችልመልኩ በቅርቡግዢው እንደወደቀሲገለጽልንላቀረብነው ረዥም ጊዜና ጉልበት አጥፍተን ላቀረብነውየግዥ ጥያቄየተሰጠው ትኩረት አነስተኛ መሆኑ ያሳያል፡፡ ኮሌጃችን የተሟላ ማሳሪያና ኬሚካል ባለመኖሩ የፈጠረብንን ክፍተት መነሻ በማድረግችግሩ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲፈታልን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የግችሩን አሳሳቢነት ያሳወቀ ቢሆንም መፍትሄ አልተገኘም፡፡የውስን ጨረታ ግዥም ቢሆንበክረምቱ መጠናቀቅ የነበረበት ሲሆን በሰበብ አስባቡ ሲጓተት ቆይቶ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የጨረታ ዶኩመንቱ ለአቅራቢዎችየተሰጠው በመጋቢት ወር ሶስተኛው ሳምንት ላይ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን ግዢ ክፍሉባለቀ ሰዓት ላይ የተለመደ መልስ እስከሚመስል ድረስ “ግዢው ወድቋል”የሚል መልስ ከመስጠትየቀረበለትን የግዢ ጥያቄከተረከበበት ዕለት ጀምሮ እንደራሱ ስራ በመውሰድና ለግዢው መሳካት ሃላፊነት በመውሰድ እንዲሰራየሚደረግበት ሁኔታ ተፈጥሮውጤታማ ግዢ እንዲከናወንካልተደረገ በስተቀር በሁሉም የኮሌጃችን የት/ት ክፍሎች ላይ ማለት ይቻላልጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠትና ተግባራዊ ምርምር ለመስራት የሚደረጉ ጥረቶችን በእጅጉ እንደሚጎዳ ሊታሰብበት ይገባል፡፡

3.5. የፊዚክስ የቤ-ተሙከራ ዕቃዎች ቆጠራ ተደርጐ እቃዎች በስርዓት ተለይተው በየስትሪም ተደራጅተዋል፣ በአሁኑ ጊዜ በሁሉም ቤተሙከራዎች የሚገኙ ኬሚካሎችና መሣሪያዎች ቆጠራ ተጠናቆ በኮምፒተር ተመዝግቦ ተይዟል፡፡ በየቤተሙከራዎች ውስጥም እንደየባህሪያቸው እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ ከአገልግሎት ውጭ የሆኑ ንብረቶች ያስከተሉትን የቦታ ጥበትና የንብረት አያያዝ ችግርን ለማቃለል ንብረቶቹን በጊዜዊነት አሰባስቦ ለማስቀመጥ የአንድ ክፍል ሽልፍ (መደርደሪያ) እንዲሰራ ተደርጎ የሚወገዱትን ንብረቶች የመለየት ስራ በመከናወን ላይ ይገኛል፡፡ የለብንን የቤተሙከራ ጥበት ለማቃለል ለ7ቱ የቤተሙከራ ክፍሎች ፓርቲሽን በማሰራት ተጨማሪ የቤተ ሙከራ ክፍሎች ማግኘት ችለናል፡፡ በየትምህርት ክፍሉ ስር ያሉ ቤተሙከራዎች ባለቤት እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር 14 የቤተ ሙከራ ኃላፊዎች (ፕሪንስፓል) በኮሌጁ የአካደሚክ ካውንስል ውሳኔ ተመድበዋል፡፡ አብዛኖዎቹም ወደስራ ገብተዋል፡፡

3.6. የቤተ ሙከራ ኮርሶች ባሉን ኬሚካሎችና መሣሪያዎች በተቻለ መጠን ጥራታቸውና መጠናቸው ተጠብቆ እንዲከናወኑ በየወቅቱ የሱፐርቪዥን ስራዎች ተከናውኗል፡፡ ከየት/ት ክፍሉ ኃላፊዎች፤ ት/ት ክፍሉ የቤተ ሙከራ ተጠሪዎች እና ኮርስ ማኔጀሮች ጋር በመተባበር በየሴሚስተሩ የቤተ ሙከራ ኮርሶች ወቅቱን ጠብቆ ፕሮግራም እንዲወጣላቸውና በወቅቱ እንዲጀመሩ ጥረት በመደረግ ላይ ሲሆን ተግባራዊ ኮርሶች ጥራታቸውና መጠናቸው ተጠብቆ ለመከናወናቸው የተለያዩ የመቆጣጠሪያና የመከታተያ ሠነዶች ተዘጋጅተው ተገባራዊ በመሆን ላይ ናቸው፡፡ ከሱፐርቪዥን ምልከታና ከመከታተያ ሠነዶች የሚሰበሰቡ መረጃዎችን መነሻ በማድረግ ከት/ት ክፍሎችሀላፊዎች፤ ቤተሙከራ ተጠሪዎች፤ የቤተ ሙከራ ረዳቶች እንደዚሁም ከመምህራን ጋር ችግሮችን ለማስተካከል የሚያስችሉ ውይይቶች ተደርጓል፡፡ ይህም በመሆኑ በወሰነ ትምህርቱ መጀመሪያ አካባቢ ተከስቶ የነበረው ተግባራዊ ትምርቶችን በወቅቱ ያለመጀመር ችግር ተስተካክሏል፡፡

3.7. በኮሌጁ ስር ያሉት የቤተ ሙከራ ክፍሎች በተቻለ መጠን ጥራታቸውን የጠበቁ የተግባር ትምህርቶች መስጫ እንዲሆኑ ለማድረግ የሚያስችል የስራ አመራር እንዲኖረው ለማድረግ የሚያስችል ረቂቅ መመሪያ (Directives) ተዘጋጅቶ የማጠናቀቅ ስራ እየተሰራ ሲሆን በቅርብ ጊዜ ውስጥ በኮሌጁ የአካደሚክ ካውንስል ጸድቆ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

3.8. ከአስር አመት በፊት በት/ት ሚኒስቴር በኩል ለኬሚስትሪ ት/ት ክፍል የመጡት የቤተ ሙከራ መሳሪያዎች ለማስጠገን ባለፉት ዓመታት የተደረጉ ጥረቶች በሙሉ ያልተሳኩ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን መሳሪያዎቹ በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ የማይሰሩ በመሆናቸው የማይሰሩትን መሳሪያዎች ተረክቦ በምትካቸው በቅናሽ ዋጋ (40% discount) አዳዲስ ሞዴሎችን ለመተካት ጅጂ ላቦግላስ (JIJE) የተባለው የሀገር ውስጥ ካምፓኒ አጅላንት ከተባለው የውጭ ካምፓኒ (Agelent company) ጋር በመተባበር ያቀረበልንን ጥያቄ መጠቀም የሚያስችለን የሰነድ ዝግጅት እየተከናወነ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የመሳሪያዎቹ ማንነትና የወቅቱ ዋጋቸው የሚያሳይ ሰነድ የዩኒቨርሲቲው የንብረት ክፍልን ጠይቀን ማግኘት ባለመቻላችን ስራችንን በወቅቱ ላለማከናወን ምክንያት ሆኖብናል፡፡ በቤተ ሙከራዎች ካይዘንን ለመተግበር ተይዞ የነበረው ዕቅድ ከታሰበው ጊዜ በላይ ዘግይቷል፡፡

የካይዘን ትግበራ በተደራጀ ሁኔታ ባይሆንም በፊዚክስ ቤተ ሙከራዎች ተጀምሯል፡፡ ካይዘንን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልገው የፓርቲሽን የመደርደሪያ ስራ መዘግየት ለካይዘን ትግበራ ዋናው ምክንያት ቢሆንም በቀጣይ ግን ለስራው ተገቢ ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት እናምናለን፡፡

## 3.9. የኮርስ አስተዳደር

ከኮርስ አስተዳደር አንፃር የበጀት ዓመቱ አንኳር ዕቅዶች ግብዓት ማሟላት (መምህራን፣ የመማሪያ ክፍል ጋር የተያያዙ፣ መጻህፍት፣ የቤተሙከራ ግብዓቶች)፣ ለማስተማሪያ ቤተሙከራዎች ኬሚካልና አንዳንድ መሳሪያዎችን በለቀማ ግዥ መግዛት፣ የትምህርት አሰጣጥ ዕቅድ (ኮርስ ጋይ ቡክ ዝግጅት)፣ የክፍል ሽፋንና የኮርስ ሽፋንን ማሳደግ፣ተግባራዊ ትምህርት (ቤተ ሙከራ፣ መስክ) መስጠት፣ ተከታታይ ምዘናና ግብረ መልስ፣ የተማሪ ውጤት በጊዜው ማሳወቅ፣ ልዩ ድጋፍ ከሚሹ ተማሪዎች በቂ ድጋፍ መስጠት፣ በተመረጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ኢ-ለርኒግ ተግባራዊ ማድረግ ነበሩ፡፡

ከግብዓት አንጻር የተከናወኑ ተግባራት የመምህራንና የቴክኒክ ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞ ቅጥር ተፈጽሟል፡፡ (ሌክቸረር 8፣ ረዳት ምሩቅ 6፣የቴክኒክ ድጋፉ ስጭ 10) ተደርጓል ፡፡ ኮሌጁ ላሉት 20 የመማሪያ ክፍሎች በ2 ዙር 400 ወንበር በመግዛት የተሰበሩት እንዲጠገኑ በማድረግ በየክፍሉ ከ65 ያላነሱ ወንበሮች እንዲሟሉ ተደርጓል፡፡ በሁሉም ክፍሎች ጥቁር ሰሌዳ የተሟላ ሲሆን፣ ለ16 ክፍሎች ነጭ ሰሌዳ ተሟልቷል፡፡

መጻህፍትን በተመለከተ ከእርዝ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ውጭ ባሉት ትምህርት ክፍሎች ላይ 1 ለ 10 እና ከዚያ የተሻለ ጥመርታ የተሟላ ሲሆን እርዝ ሳይንስ ትምህርት ክፍል ላይ አሁንም የጎላ የመጽሀፍት ተማሪ ጥመርታ ጉድለት አለ፡፡ ለአብዛኞቹ ኮርሶች ሶፍት ኮፒ መጽሀፍትም አልተገኙም፡፡ መጽሐፍትን በግዥ ለማሟላት ጥረት እያደረግን ቢሆንም በማዕከላዊ የግዥ ኬዝ ቲም እየተከናወነ ያለው የግዥ ሂደት ከተገቢው በላይ ጊዜ የወሰደ ከመሆኑም በተጨማሪ የተወሰኑ መጽሐፍትን በኮሌጅ በኩል ለመግዛት ያደረግነው ጥረት በማዕከላዊ የግዥ ኬዝ ቲም ትዕዛዝ እንዲቋረጥ የተደረገ በመሆኑ ያሳደረብን ተጽዕኖ ሊጤንና አፋጣኝ እርምጃ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

በየወሰነ ትምህርቱ መጀመሪያ ላይ አስቀድሞ የማስተማሪያ መርሀ ግብር በማውጣት የኮርስ አሰጣጥ ዕቅድ (ኮርስ ጋይድ ቡክ) ማዘጋጀት፣ በስርዓተ ትምህርቱ መሰረት በተግባር የተደገፈ ትምህርት መስጠት፣ ኮርሶችን ሙሉ በሙሉ መሸፈን፣ በኮርስ ጋይድ ቡክ መሰረት ተከታታይ ምዘና መስጠትና የምዘና ግብረ መልስ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ውስጥ መስጠት የየኮርሱን ውጤቶች ከdeadline በፊት ለሬጅስትራር ማስገባት ላይ ትኩረት አድርገን ስንሰራ የቆየን ሲሆን፣ በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት አፈጻጸማችን በጣት የሚቆጠሩ (ከአምስት የማይበልጡ) ኮርሶች ሳይጠናቀቁ ከመቅረታቸው ውጭ የኮርስ ሽፋናችን አጥጋቢ ነበር፡፡ ተከታታይ ምዘናም ቢሆን በኮርሱ ዕቅድ መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ ባይከናወንም አበረታች ነበር፡፡

የምዘና ግብረ መልስ ቢበዛ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለመስጠት አቅደን የነበር ቢሆንም በአመዛኙ አልተሳካልንም፡፡ ሆኖም ካለፉት ዓመታት ጋር ሲወዳደር ከጥቂት ኮርሶች በስተቀር ዘግይቶም ቢሆን ግብረ መልስ የመስጠት ጅምሩ አበረታች ነው፡፡ በኮሌጁ በየትምሕርት ፕሮግራሙ ካሉ የሴክሽን የተማሪ ተወካዮች

ጋር የትምሕርት ግብዐቶችን አቅርቦት፣ የኮርስ አሸፋፈን፣ የተግባራዊ ትምህርት አሰጣጥ፣ የተከታታይ ምዘና፣ የምዘናዎች ግብረ መልስ አሰጣጥና የPeer-Led Learning አፈጻጸም በተመለከተ መደበኛ ውይይት ስናደርግ የከረምንበት ወቅት ሲሆን ከተማሪዎች በቀረበው መሰረትና በኮሌጁም ክትትል መረዳት የተቻለው የኮርስ አሸፋፈንና ተከታታይ ምዘና ከጊዜ ወደ ጊዜ አበረታች መሻሻል እያሳየ መምጣቱን ነው፡፡ የየኮርሱን ውጤቶች ከdeadline በፊት ለሬጅስትራር ማስገባት ላይ አፈጻጸማችን ሙሉ ነበር፡፡ በያዝነው ወሰነ ትምህርት የእያንዳንዱ ኮርስ አሸፋፈን፣ ተከታታይ ምዘናና ግብረ መልስ በየሳምንቱ መደበኛ የጽሁፍ ሪፖርት እየቀረበባቸው በአካዳሚክ ካውንስል ውይይት ስለሚደረግባቸው በመሆኑ ከፍተኛ ውጤት ይጠበቃል፡፡

## 3.10. የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞችን ማስፋፋት

በኮሌጁ በአሁኑ ጊዜ አምስት የሁለተኛ ዲግሪ (በባዮሎጂ፣ ኬሚስትሪ፣ ሒሳብ፣ ፊዚክስና ማቴሪያል ሳይንስ የተለያዩ ስፔሺያላዜሽኖች) እና በአንድ የሶስተኛ ዲግሪ (ዶክትሬት ዲግሪ በስፔስ ፊዚክስ መስክ) መርሐ ግብሮች በማሰልጠን ላይ ይገኛል፡፡ ኮሌጁ የድህረ ምረቃ ትምህርትን ለማስፋፋት በርካታ ዕቅዶች ያሉት ቢሆንም ከስኬት አንጻር ብዙ ይቀራል፡፡

የሂሳብ የሶስተኛ ዲግሪ ስርዓተ ትምህርት (በተለያዩ ስፔሺያላዜሽኖች) ባለፈው ዓመት ተዘጋጅቶ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ አውደ ጥናት ተካሂዶና በኮሌጁ አካዳሚክ ካውንስል ጸድቆ ለካሪኩለምና ስታንዳርድ ኮሚቴ የቀረበ ሲሆን በትምህርት ክፍሉ ካለው የመምህራን የመቀበል አንጻር ታይቶ የዘገየ ቢሆንም ውሳኔ በመጠባበቅ ላይ ነን፡፡ በባዮሎጂ Botanical Sciences ስርዓተ ትምህርቱ የተዘጋጀ ሲሆን አውደ ጥናት ለማካሄድ ዝግጅት እየተደረገ ነው፡፡ Applied Microbiology እና Condensed Matter Physics የሶስተኛ ዲግሪ ስርዓተ ትምህርቶች በቀረጻ ላይ ናቸው፡፡

በማስትሬት ዲግሪ ደረጃ Applied Genetics እና Statistics በግንቦት ወር መጀመሪያ ላይ የስርዓተ ትምህርት ክለሳ አውደ ጥናት ይካሄዳል፡፡ Environmental Sciences ስርዓተ ትምህርት በመዘጋጀት ላይ ነው፡፡ Aquatic Resource Biology and Management ባለፈው ዓመት ቀርቦ ከግብርናና አካባቢ ሳይንስ ኮሌጅ ጋር በነበረው አለመግባባት ስርዓተ ትምህርቱ ከመጽደቅ ዘግይቷል፡፡ ሆኖም ስልጠናው ውሃማና እርጥበት አዘል ከሆነው አካባቢያችን አንጻር አስፈላጊ በመሆኑ አፋጣኝ ውሳኔ ሊሰጥበት ይገባል፡፡

## 3.11. ምርምር

## በሂደት ላይ ያሉ ምርምሮች

በኮሌጁ በአሁኑ ጊዜ 61 (ድግግሞሹን በመተው) መምህራን ተሳታፊ የሆኑባቸው 29 የምርምር ስራዎች በሂደት ላይ ናቸው፡፡ ከዚህ ውስጥ 9ኙ በ2004፣ 8ቱ በ2005 እና 12ቱ ደግሞ በ2006 የተጀመሩ ናቸው፡፡ በ2004 እና በ2005 የተጀመሩ የምርምር ስራዎችን በዚህ ዓመት ለማጠናቀቅ ክትትል እያደረግን ነው፡፡ ለኮሌጁ ለ2006 በጀት ዓመት የምርምር ማስኬጃ ብር 650, 000 ተመድቦልን የነበረ ሲሆን በ2004 እና 2005 በጀት ዓመት ተጀምረው ሳይጠናቀቁ ለቀሩ ምርምሮች ማስጨረሻ ባቀረብነው የተጨማሪ በጀት ጥያቄ መሰረት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት በመደበልን ብር 278 434 ተጨማሪ በጀት የተጀመሩ ምርምሮች እየተካሄዱ ነው፡፡ ሆኖም ለ2006 በጀት ዓመት ተመድቦልን የነበረው በጀት በጣም አነስተኛ ስለነበር አቅም ባላቸው ተመራማሪዎች ቀርበው የነበሩ የምርምር ሃሳቦችን ሁሉ በበጀት ማነስ ምክንያት ለመቀነስ የተገደድንበት ሁኔታ በመኖሩ ለወደፊት የምርምር በጀት አመዳደቡ የኮሌጆችን የምርምር አቅም ያገናዘበ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል፡፡

## የታተሙ የምርምር ስራዎች

በኮሌጁ በ2013/2014 29 ብቻ የምርምር ስራዎች ታዋቂነት ባላቸው አገር ዓቀፍና አለም አቀፍ አታሚዎች ታትመዋል፡፡ ይህ አሃዝ መምህራን ከጊዜ ወደ ጊዜ ለምርምር እየሰጡ ያለውን ትኩረት ያሳያል፡፡ ዩኒቨርሲቲያችን እስከ 2017 በአፍሪካ ካሉ ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች አንዱ ለመሆን ይዞ የተነሳውን ርዕይ ለማሳካት በፍጥነት እየተጓዘን ስለመሆኑም አመላካች ነው፡፡ ሆኖም በኮሌጁ ካለ እምቅ አቅም አንጻር ሲታይ አሁንም ምርምርን ከማበረታታት አንጻር ብዙ መሰራት እንዳለበት እሙን ነው፡፡

## Ethiopian Journal of Science and Technology (EJST)

ኮሌጃችን ከምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት የተረከበውን Ethiopian Journal of Science and Technology (EJST) አደረጃጀት ከማሻሻልና ሕትመት አጠናክሮ ከማስቀጠል አንጻር ለጆርናሉ Editor-in-Chief መሾም፣ ተባባሪ ኤዲተሮችን መርጦ መሰየም፣ አማካሪ ቦርድ ማቋቋም፣ የጆርናሉን አደረጃጀትና አሰራር አጥንቶ ማስፈቀድ፣ የቢሮ አደረጃጀት መስራትና ማቋቋም፣ አስፈላጊ ሰራተኞችን ለመመደብ መዋቅር ማስፈቀድና መመደብ፣ ጆርናሉ በዩኒቨርሲቲው ዕውቅና እንዲኖረው ማድረግ እንዲሁም የምርምር ሥራዎችን እየተቀበሉና እየገመገሙ ማሳተም የሚሉ ተግራትን አቅዶ ሲንቀሳቀስ ቆይቷል፡፡

በዚህም መሰረት ከኮሌጁ አንጋፋ ተመራማሪዎች መካከል በመምረጥ Editor-in-Chief የተመደበ ሲሆን 11 አባላት ያሉበት ተባባሪ ኤዲተሮችንና 30 አባላት ያሉት የአማካሪ ቦርድ አቋቁሟል፡፡ የጆርናሉን አደረጃጀትና አሰራር በተመለከተ ኤዲቶሪያል ፖሊሲ ተዘጋጅቶ በተባባሪ ኤዲተሮች አስተያየት እተሰጠበት ይገኛል፡፡ ፖሊሲው በሌችም የኮሌጁ ተመራማሪዎች አስተያየት ከተሰጠበት በኋላ ለኮሌጁ አካዳሚክ ካውንስል ቀርቦ የሚጸድቅ ይሆናል፡፡ ይህን ተከትሎም ጆርናሉ በዩኒቨርሲቲው ዕውቅና እንዲኖረው የማድረግ ስራ በቀሪ ወራት ይሰራል፡፡ ጆርናሉ ቀደም ሲል ምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት ይተዳደር ከነበረ ጊዜ ጀምሮ የቀረቡ የምርምር ስራዎች የሪቪው ስራ እየተጠናቀቀ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሕትመት ይቀርባል፡፡

ከዚህ ጋር የቢሮ አደረጃጀት መስራትና ማቋቋም በዕቅድ ተይዞ የነበረ ቁልፍ ተግባር ቢሆንም ቢሮ ባለመገኘቱ ምክንያት እስካሁን ራሱን የቻለ አደረጃጀት የለውም፡፡ ሆኖም ከስራው ቀጣይነትና ከሚኖሩት የተለያዩ መረጃዎች ደህንነትና የአሰራር ነጻነት አንጻር አሁንም ለጆርናሉ አንድ ቢሮ የመመደብ ጉዳይ ትኩረት ይሻል፡፡

## ሁለተኛው ዓመታዊ የሳይንስ ኮንፈረንስ

ዕውቅ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን ያለንን ርዕይ ዕውን የምናደርግበት አንዱ መንገድ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ የምርምር አውደ ጥናቶችንና ኮንፈረንሶችን ማካሄድ መሆኑን የተረዳው ኮሌጃችን ባለፈው በጀት ዓመት “Philosophy and Excellence in Science, What is Science for” በሚል መሪ ቃል የመጀመሪያውን ዓመታዊ ኮንፈረንስ በከፍተኛ ስኬት አካሂዷል፡፡ የመጀመሪያውን ዓመታዊ የሳይንስ ኮንፈረንስ ስኬት እንደተሞክሮ በመጠቀም በዚህ ዓመት “Science, Sustainable Development and Global Challenges” የሚል ወቅታዊ መሪ ቃል የያዘ ዓመታዊ ኮንፈረንስ ለማዘጋጀት አቅደን ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ኮንፈረንሱ ከሚያዝያ 24-25 ቀን 2006 ዓ.ም የሚካሄድ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ቅድመ ዝግጅቱ በመጠናቀቅ ላይ ነው፡፡ ኮንፈረንሱን ያለምንም ችግር በስኬት ለማጠናቀቅ የተለያዩ የኮሚቴ አደረጃጀቶችን ፈጥረን በመስራት ላይ እንገኛለን፡፡ በዚህ አጋጣሚ የኮሌጁ መምህራን በመጀመሪያው ዓመታዊ የሳይንስ ኮንፈረንስ በባለቤትነት ስሜት ላደረጉት ንቁ ተሳትፎና በዚህ ዓመት ለሚደረገው ኮንፈረንስም እያሳዩ ያለው ፍላጎትና እያደረጉ ያለው ጥረት ምስጋና ሊቸራቸው ይገባል፡፡ ከ150 ያላነሱ የምርምር ወረቀቶች በኮንፈረንሱ ለመቅረብ የተላኩ ሲሆን ካለው የማቅረቢያ ጊዜና ገንዘብ አንጻር የተሻሉ 60 የምርምር ወረቀቶች ተመርጠዋል፡፡ ካለፈው ዓመቱ ኮንፈረንስ በተለየ መልኩ በዚህ ዓመት ተቀባይነት ካገኙ 60 የምርምር ወረቀቶች መካከል 50 በመቶ የሚሆኑት በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎች የቀረቡ መሆኑ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ ለምርምር የሰጠውን ትኩረት ያሳያል፡፡

ለኮንፈረንሱ ማስኬጃ ገንዘብ ለማሰባሰብ ንድፈ ሃሳብ ተዘጋጅቶ የስፖንሰር አፈላላጊ ቡድን ተልኮ ገንዘብ ለማግኘት ጥረት የተደረገ ቢሆንም እስካሁን ተጨባጭ የሆነ አበረታች ውጤት አልተገኘም፡፡ ሆኖም ተስፋ የሰጡን አካላት ስላሉ ክትትል እያደረግን ነው፡፡ ኮሌጃችን ካለው በጀት የሚንቀሳቀስ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር በኩልም ድጋፍ እንደሚደረግልን ተስፋ አለን፡፡

ኮንፈረንሱን አካሂደን እንዳጠናቀቅን የኮንፈረንሱን ሂደት፣ የተገኙ ውጤቶችንና ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን በመገምገምና ማጠቃለያ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቀጣይ ኮንፈረንስ መነሻ ሃሳብ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡ የኮንፈረንሱን Proceeding የማሳተም ስራም ይሰራል፡፡

## ሳምንታዊ ሴሚናር

በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት 12 እና በሁለተኛው ወሰነ ትምህርት 9 በድምሩ 21 ወረቀቶች ቀርበዋል፡፡ ሂሳብና ፊዚክስ ላይ ከአስተባባሪዎች መቀየር ጋር ተያይዞ ተቀዛቅዞ የቆየ ቢሆንም አሁንም መነሳሳቱ አለ፡፡ ኬሚስትሪ ት/ክፍል በመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት የቀረበው አንድ ጥናት ብቻ ሲሆን በሁለኛው ወሰነ ትምህርት በተጠናከረና በፕሮግራም በሚመራ አሰራር እየተመሩ በመሆኑ እስካሁን 4 ጥናቶች የቀረቡ ሲሆን በቀጣይም ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡ ሳምንታዊ ሴሚናሮች ላይ ያለው የመምህራን ተሳትፎ ከሚጠበቀው በታች በመሆኑ በቀጣይ ጊዜያት ተሳትፎን ለማሻሻል እንሰራለን፡፡

### 3.12. ማኅበረሰብ አገልግሎት

በኮሌጁ በዚህ ዓመት ከመቼውም ጊዜ በተሻለ ሁኔታ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች ላይ ለመሳተፍ ከፍተኛ መነቃቃት አለ። ሁሉም ትምህርት ክፍሎች በርካታ የማኅበረሰብ አገልግሎት የትኩረት አቅጣጫዎች (Thematic Areas) ተለይተው እየተሰሩ ሲሆን የስራ አመራሩን የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት በባለቤትነት ወስዶ እየሰራው በመሆኑ ለኮሌጁ ለክትትል አመቺ አልሆነም። አንዳንድ መምህራን ሂደቱን ሪፖርት ለማድረግ ፈቃደኝነት እስከማጣት ደርሰዋል። በመሆኑም የስራ አመራሩ ለኮሌጆች መሰጠት ይኖርበታል። (የታቀዱና በመሰራት ላይ ያሉ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራዎች በተመለከተ ዝርዝር ሪፖርቱ ከዚህ በታች በቀረበው የፊዚካል ስራዎች አፈጻጸም ሪፖርት ማቅረቢያ ሰንጠረዥ ተካቷል)

## IV. በእቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

አንዳንድ መምህራንና ሰራተኞች ግፊት ካልተደረገ በስተቀር የትምህርት ፕሮግራሙ ጉዳይ የእኔ ጉዳይ ነው ብሎ በተነሳሽነት መሥራት ላይ ጅምሩ ቢኖርም ብዙ ይቀራል።

በማቴሪያል አቅርቦት ረገድም ከፍተኛ የሆነ የመማሪያ ክፍል እና የመምህራን ቢሮ እጥረት ያለ በመሆኑ ትኩረት ይሻል።

አሁን በዋናው ግቢ ደረጃ ያለው የፋይናንስ አስተዳደር አሰራር የግቢው ሁሉም ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች በጀት በአንድ ላይ ተቀላቅሎ ወጭ የሚደረግ በመሆኑና የበጀት አጠቃቀም ሽሚያ በመኖሩ ኮሌጃችን ተግባራቱን ባወጣው ዕቅድ መሰረት ለመስራት ተቸግሯል፣ አንዳንድ የወጭ መደቦች ላይ ስራው ሳይሰራ ገንዘብ አለቀ የሚባልበት ሁኔታ እየተፈጠረ በመሆኑ አስቸኳይ መፍትሄ ይሻል።

የግዥ፣ ጥገናና ትራንስፖርት አገልግሎቶች አሰጣጦች ላይ አሁንም ያልተፈታ ከፍተኛ ችግር አለ።

## V. ለወደፊት ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

የሳይንስ ኮሌጅ አንዱ መለያ የሆነው ጉዳይ ተማሪዎች በቤተ ሙከራ ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ በመሆኑ ቤተ ሙከራዎችን ካይዘንን ተጠቅሞ በሚገባ ማደራጀትና ኬሚካልና መሳሪያዎች የተማሉና ጤንነታቸው የተጠበቀ ማድረግ በቀጣይ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሰራ አንዱ ዐቢይ ተግባር ነው። ቀጣዩ ጊዜ የዓመቱ መጨረሻ እንደመሆኑ የተመራቂ ተማሪዎችን ማህደር በማጣራት መመረቅ ያለበት አንድም ተማሪ ሳይቀር በጊዜው ለማስመረቅና ማስረጃ ለመስጠት እንተጋለን። ከዚህ ጋር ተያይዞ የሥራ ፈጠራ ስልጠና የመስጠትና ሞዴል የመጫ ፈነታ የመፈተን ተግባራት መከናወን ይኖርባቸዋል። በዚህ ረገድ

ተጀምሮ እልባት ያላገኘውን ግዥ ዳር ማድረስ ይኖርብናል፡፡ ኮርሶችን በሙሉ በተገቢው መሸፈን፣ ተከታታይ ምዘናና ግብረ መልስ በትኩረት የሚሰሩ ተግባራት ይሆናሉ፡፡

ሌላው ትኩረት የሚሻው ጉዳይ አሁን በጥሩ አቋም ላይ የሚገኙትን የመመመ ዱብኖች አሰራር አጠናክሮ ማስቀዐልና ወደ ሥራው ተጠናክረው ያልገቡትን ተገቢ ድጋፍ በማድረግ እንዲገቡ ማድረግ ይሆናል፡፡

ተጀምረው ያልተጠናቀቁ የቅድመና ድህረ ምረቃ ስርዓተ ትምህርቶችን ማጠናቀቅ ሌላው ዓቢይ ጉዳያችን ይሆናል፡፡ ኮሌጃችን ከምርምርና ማኅበረሰብ አገልግሎት ም/ፕ/ጽ/ቤት የተረከበውን Ethiopian Journal of Science and Technology (EJST) አደረጃጀትና ኤዲቶሪያል ፖሊሲ በማጠናቀቅ በዩኒቨርሲቲው ዕውቅና እንዲኖረው የማድረግ ስራና ሁለተኛውን ዓመታዊ የሳይንስ ኮንፈረንስ በስኬት ማጠናቀቅ የትኩለት አቅጣጫዎቻችን ይሆናሉ፡፡

## VI. ማጠቃለያ

ያለፉት ዘጠኝ አፈጻጸም ሲታይ ሞጁላር የትምህርት አሰጣጥን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ተከታታይ ምዘናና ተግባር ተኮር የትምህርት አሰጣጥ ላይ አበረታች የሆኑ ለውጥ አለ፡፡ ሆኖም ግብረ መልስ ላይ ወደ 1ላ የመቅረት ጉዳይ ስላለ አሁንም የኮሌጁ የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል፡፡ ምርምርን በመስራትና በማሳተፋ ረገድ መልካም የሆነ መነሳሳት አለ፡፡ በተሻለ በጀት ቢደገፉ የተሻለ የምርመር ውጤት ማየት ይቻላል፡፡ አገልግሎት ላይ በርካታ መምህራን ተሳታፊ የሆኑበት ዓመት በመሆኑም ካለፈው ዓመት በተሻለ መልኩ የማህበረሰብ አገልግሎት ዘርፎችም ሰፊ ነው አብዛኞቹ ማስተማር ላይ ብቻ ያተካሩ በመሆናቸው የትኩረት አቅጣጫዎች ለይቶ መንቀሳቀስ ይገባል፡፡

በኮሌጁ ውስጥ በተለያዩ ደረጃዎች የተፈጠሩ የመመመ አደረጃጀቶች ወደ ስራ ገብተዋል፡፡ እነዚህ ቡድኖች የትምህርት ጥራትን ለማሳደግና ምርመርና ማህበረሰብ አገልግሎትን ለማበረታታት ያለው ድርሻ ጉልህ በመሆኑ አጠናክረን መቀጠል ይኖርብናል፡፡ ተጨባጭ ዕቅድን መሠረት አድርገን ተጨባጭ ተግባራትን መፈፀምና ተጨባጭ ሪፓርት ማድረግ መለመድ የኖርበታል፡፡

# VII. የሳይንስ ኮሌጅ የ2006 በጀት ዓመት ዘጠኝ ወራት የፊዚካል ዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት

| ግቦች | መለኪያ | መድረሻ (ግብ ) | መግለጫ |
|---|---|---|---|
| **እይታ 1. ደንበኛ** | | | |
| **ግብ 1.1 የመምህራንን እርካታ በማረጋገጥ በኮሌጁ ውስጥ ያላቸውን ቆይታ ማስረዘም** | | | |
| **ተግባር** 1. የመምህራን የቢሮ ችግር መፍታት፣ | መቶኛ | 100 | አልተፈታም |
| **ተግባር** 2. ግዥ በማናወን የመምህራንን የወንበር፣ የጠረጴዛና የኮምፒዩተር ፍላጎት ማሟላት | መቶኛ | 100 | አልተፈጸመም፡፡ ምክንያቱም ግዥው የተጠየቀ ቢሆንም ግዥ በማዕከል ይፈጸማል ተብሎ ስለታገደ |
| **ተግባር** 3. ከመምህራን ለሚነሱ ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ግልጽና አፋጣኝ (በ2 ቀናት ውስጥ) ውሳኔ በመስጠት እርካታን ማረጋገጥ | መቶኛ | 95 | ከሁለት ቀናት በላይ ሊዘገይ ቢችልም ሕጋዊ ጥያቄዎች መፍትሄ አግኝተዋል |
| **ተግባር** 4. በመምህራንና ሠራተኞች ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ለከሌጁ መምህራንና ሰራተኞች የሽርሽርና የመዝናኛኛ ፕሮግራም እንዲኖር ማድረግ (Social event ማካሄድ) | ቁጥር | 1 | አልተከናወነም |
| **ተግባር** 5 የአካዳሚክ ስታፍን የእድገት መመሪያና ደንቦች መሰረት በማድረግ መምህራንና ቴክኒካል አሲስታንቶች እድገት እንዲያገኙ ማድረግ | ቁጥር | አሟልተው የቀረቡትን በሙሉ | አሟልተው የቀረቡትን በሙሉ ተሰጥቷቸዋል |
| **ግብ** 1.2 **ተማሪዎችን መመዝገብ** | | | |
| **ተግባር** 1 ቅድመ ዝግጅት በማድረግ አዲስ ተማሪዎችን ተቀብሎ የህይወት ታሪክ ፎርም ማስሞላት | መቶኛ | 100 | 464 ቅድመ ምረቃና 35 ድህረ ምረቃ ተማሪዎችን ተቀብለናል፡፡ |
| **ተግባር** 2 አዲስ ገቢ ተማሪዎችን በየፕሮግራሙ ሴክሽን መመደብና መታወቂያ መስጠት | መቶኛ | 100 | በየሴክሽን ተመድበው መታወቂያ ተሰጥቷቸዋል |

| | | | |
|---|---|---|---|
| **ተግባር** 3 አዲስ ገቢና ነባር ተማሪዎችን መመዝገብ | መቶኛ | 100 | ምዝገባው ተከናውኗል |
| **ተግባር** 4 የነባር ተማሪዎችን ዉጤት አጠናቅሮ ያለፉትን መመዝገብ | መቶኛ | 100 | ተከናውኗል |
| **ግብ 1.3 የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ** | | | |
| **ተግባር** 1. ከተማሪ ተወካዮች ጋር በየሶስት ሳምንቱ መደበኛ ውይይት በማድረግና በመማር ማስተማር ዙሪያ ያሉባቸውን ችግሮች በመለየት መፍትሄ መስጠት | የእርካታ መጠን | 95 | በመደበኛነት እየተካሄደ ነው፡፡ |
| **ተግባር** 2. የተማሪዎች ተወካዮች ተማሪ ተኮር በሆኑ ውሳኔዎች እንደሳተፉ ማድረግ | ድግግሞሽ | | በአካደሚክ ካውንስል ስበሰባዎች የተማሪ ተወካዮች ይገኛሉ |
| **ተግባር** 3 ለመጀመሪያ ዓመት የሳይንስ ቅድመና ድህረ ምረቃ ተማሪዎች አጠቃላይ የላብራቶር ህግና ደንብ/ሴፍቲ/ ስልጠና መስጠት | ቁጥር | 1 | አልተከናወነም |
| **ተግባር** 4 ለአንደኛ አመት ተማሪዎች ኦሪየንቴሽን መስጠት | ቁጥር | 1 | ስለ ሞጁላራይዜሽን፣ አካደሚክ ሬጉሌሽንና የተማሪ መማር፣ መመራመርና መተግበር ቡድኖች ዓላማና አተገባበር የተመለከተ ኦሬንቴሽት ተሰጥቷል |
| **ግብ 1.4 የተማሪዎችን እርካታ ማረጋገጥ** | | | |
| **ተግባር** 1. ከፍተኛ ዉጤትና ልዩ ፈጠራ ላስመዘገቡ ሴትና ወንድ ተማሪዎች እውቅና መስጠት | ድግግሞሽ | 1 | አልተከናወነም |
